# ደም መገበርን ተለማመድነው ?

በሃገራችን ኢትዮጵያ ፍትህ ሰላም እኩልነት ብልጽግና እንዲሰፍን የሃገራችን ሉዓላዊነትና አንድነት እንዲጠበቅ በተደረገው ትግል ውስጥ ህይወታቸው ያሳለፉ የሰጡ ዜጎቻችን በቁጠር ምን ያህል እንደሆን? ይህ እንጊዲህ እንደሃገርና ህዝብ ቆመን በፖለቲካ ሳቢያ ብቻ ያለፈውን ህይወት ማለቴ ነው። ከንጉሱ ጀምረን በደርግና በህዋሓት（ኢሃዴግ）ዘመን የተሰዋው ህይወት ቁጥር ምንያህል ነው? መቶ ? አንድሽህ ?መቶ ሽህ ?ሚሊዮን ? ማን ያውቀዋል?

አዎ ፍትህ በሌለበት ነጻነት በሌለበት ፍትህንም ሆነ ነጻነትን ለመግኘት መስዋእትነትን መክፈል የህብረተሰብ ህልውናና እድገት ውስጥ የሚታይ ክስተት ነው። ዛሬ በሰለጠኑት ሃገሮች አንዲት ነፍስ ዋጋዋ እጅግ በጣም ቢዙ ነው። በአደጋና አልፎ አልፎ ከከፋት ከሚመነጭ የግለሰቦች ባህርይ የተነሳ ህይዎት ይጠፋል ያም ቢሆን የጠፋው የእያንዳንዱ ሰው ህይወት ቀሪውን ሊያድን በሚችል ህጋዊና ሚዋችንም በከንቱ የማያስቀር በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ፈሶበት ተገቢውን ምርመራና የምርመራውም ውጤት ለህዝብ ይታውቃል። የሃገርችውን ጥቅም ለማስጠበቅ በጦርነት የወደቁ ከ 40 ና 50 አመት በሁዋላም ቢሆን አጽማቸውና ታሪካቸው በክበር እንዲያርፍ ይደርጋል። በምንም መልኩ ቢሆን ሃገራችንን ለማነጻጸር ፈልጌ አይደልም።

አባቶቻችን ከቅኝ ገዚዎችና ወራሪዎች ጋር ባደረጉት ተጋድሎና በኛ ዘመንም ሃገራችን አትቆረስም ብለው በኤርትራ በረሃና በትግራይ የረገፉት የኢትዮጵያ ሊጆች ከጭቆና ለመላቀቅ መገንጠል ነጻነትን የሚያጎናጽፍ መስሎአቸው በኤርትራ ተራሮች የወደቁት ኤርትራውያን (ለእኔ ኢትዮጵያውያን) በትግራይ መጀመሪያ በትግራይ ነጻነት ስም በሁዋላም በእትዮጵያ የዲሞክራሲና የብሄረሰብ እኩልነት ስም የወደቁት የትግራይ የአፋር የሲዳማ የወላይታ የከምባታ በአጥቃላይም የደቡብ ልጆች በኦኤጋዴን በረሃ የወደቁት የኢትዮጵያውያን ሶማሌ ሊጆች የጋምቤላ የቤንሻንጉልና የህዝባቸው ቁጥር ትልቅነት ተሳትፎአቸውንም ሆነ መስዋእትነታቸውን የበለጠ እንዲያደግ አድርጎታል የመጣው ፖለቲካ ሁሉ ዋነኛ ሰለባ የሆኑት ዛሬም እየሆኑ ያሉት የኦሮሞና የአማራ ልጆች በድምሩ በውብ ቁዋንቋና ባህል የተዋበችው የአንዲት የኢትዮጵያ ደም ክፋይ ልጆች ናቸው ። በቅይሽብር በነጭ ሽብር በተገንጣይ በአስገንጣይ በሽብረተኛነት በጎጠኝነት ፖለቲካ ያለቁት ምን ያህል ይሆኑ?

ሁሉም በየጎራው የከፈሉትና የገበሩት ድም የተሻለ ሃገርና የተሻለ የህዝብ ህይወት ፈጥሩ? ወይስ ገና አሁንም የፈሰሰው ድም አልበቃምና ለሌላ ግብር እየተዘጋጀን ነው? እኮ ለምንድነው ያን ያህል ህይወት የገበርነው? የተገበረው ህይወት "ወላድ በድባብ ትውጣ" የሚያስብል ነው ለውጥም አላመጣንም ማለት ግን አይደለም ። በርግጥ ቀድሞም በየዋህነትም ይሁን በአስተሳሰብ ዝቅተኝነት ጥቂቶች የራሳቸው ያደርግዋት ሃገርና ህዝብ ዛሬ ሳይንሳዊ ትንተና በሚሰጣቸው የፖለቲካ መገለጫዎች አሽብርቀው የህብረተሰቡን ስጋውን ሳይሆን ነፍሱንም ጭምር እይተቆጣጠሩት ያሉበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ጥቂቶች የእኛ የሚሉዋትን ሃገር እየገነቡ ነው።

ብዙሃኑ ግን ቢችገርም በተስፋዋ የሚኖርባትን ሃገርም ባለቤትነቱን ተነጥቆ የበይ ተመልካች ሆኖአል። ታዲያ ይህ ሁሉ ድም የፈሰሰለት ሃገር ህዝብ ለሱ የሞተለትንና የሚከፈልለትን ዋጋ ተገናዝቦአል? ቢያንስ ለኔ ሲል ነው የሞተልኝ ይላል ወይ? የሞቱለቱን ልጆቹን ፍሬ በልቶ ለማጣጣም እንጂ ፍሬውን ለመንከባከብ የማይችል ከሆነና ነጻነቱን የሚለካው በየቀኑ ሰልፍ እየወጣ ዛሬ ይህን

ያህል ሞተ ብሎ የሚያርፍ ከሆነና ፖለቲከኞቻችንም ለውጥንና መስዋእትነትን ይህን ያህል ሰው ሞተ እያልን አስከሬን በመቁጠር ፌስ ቡክ በማድመቅ ዝናችንን ከመገንባት ያለፈ ለውጥ የማናመጣ ከሆነ ህጻናቱ ለምን ዪሙቱ ? ገዳዮች በደም መፍሰስ በመግደል በማሰር በማሰቃየት ሃገርን ከጥፋት ለማዳን ነው የሚል አንዱን እየገደልክ ሌላውን የማዳን የድንቁርናና የእብሪት ፖለቲካ ሲጨፍሩ እያየን ወደፊት ስንት ደም እንዲፈስ እያዘጋጀን ነው? ከአዕምሮአችን ማስወገድ መግደል ማጥፋት መጠፋፋት መደምሰስ ወዘተርፈ 。。 ከታሪክ ከመረጃ ከጥናታዊ ፍልስፍና ከተጨባጭ ከወቅቱ ሁኔታዎች የሀገሪቱን ጥቅም በማይጻረር መወያየት መነጋገር መቻቻል መተራረም መወቃቀስ ልህዝብ ጥቅም ሲባል ስጥቶ መቀበል የሚሉት በጎ መንፈሶች የሚያርፉብን መቼ ነው?

በፖለቲካ ሳቢያ መገዳደል ምንጩ ሁዋላ ቀርነትና ከፍተኛ ተጠቃሚነት ፍላጎት ነው። ዛሬም ንጽሃን ህጻናት ሰለባ እየሆኑ ያሉት ለዚሁ ነው። ገዳዮችም አስገዳዮችም በህዝብ ስም የመነግድ ችግራችንን በአንድ አላም አብረን ከተሰለፍነው ጋር እንኳን ቁጭ ብለን የመነጋገር ድፍረቱ የሌለን የራሳችንን ተክለሰውነት እንጂ የእያንዳንዱ ሰው ህይውት ግድ የማይለን ፖለቲከኞች ነን ።

ህብረተሰባችንም ብፖለቲካ ሳቢያ ሞትን አለማምደነዋል። ያማ ባይሆን እንኳን መቶ ሰው በግፍ ተገድሎ አንድም ህይወት ቢሆን አይቀሬውን ህዝባዊ ማእበልን ያመጣል። ዛሬም በየፌስቡኩ ፊታችን የሚያበራውን ፎተግራፍ እየለጠፍን ሚስኪን ደሃውን አቅጣጫውን በማያውቀው ፖለቲካ ውስጥ ድሙን ለሰይጣኖች（ለዕምበለ ስብ） እንዲገብር ከማድረግ ይልቅ የጎደለንና ትግሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል እንዲሆን በማድረግ የማንኛውም እትዮጵያዊ ደም ዋጋ ያለው መሆኑን የተገነዘበን የተደራጀ ህዝባዊ መሰረት ያለው የፖለቲካ ስብስብና ራእይ ሊቀድም ይገባል። ለጥቂት የህዋሃት የኦፒዶ የብአዴን የደቡብ ቅምጥሎች ወይም ተቃዋሚ ነን ብለው በንዲህ አይነቱ ሃገራዊ አደጋ ጊዜ እንኳን ሊዩነታችውን በማቻቻል ሃገራዊ አጀንዳ መቅረጽ ላልቻሉ የስልጣን ጥመኞች አንዲት ህይወት መገበር የለበትም ።

በተጨመላለቀ የፖለቲካ አስተሳሰብ የሚገበር ህይወት ከንቱ ሆኖ እንዳይቀርና ዉጤታማ እንዲሆን የጎደለንን የመሪ ፖለትካ ድርጅት በምንም መልኩ ማምጣት አጣዳፊ ተግባር ሊሆን ይገባል።

Gishag70@yahoo.com